የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት
HOUSE OF PEOPLES REPRESENTATIVES OF THE FDRE

7ኛው የኢፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በ1ኛ ዓመት የሥራ ዘመኑ መስከረም 25 ቀን 2019 ዓ.ም የመንግሥት ምስረታ ስነ ሥርዓት አካሂዷል፡፡

በዚሁ ዕለት ምክር ቤቱ የኢፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባኤንና ምክትል አፈ ጉባኤን ሹመት አጽድቋል፡፡

በዕለቱ ክቡር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)ን የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር አድርጎ ሰይሟል፡፡

በተያያዘም ክቡር አቶ ተመስገን ጥሩነህን የኢፌዴሪ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ሹመት ጨምሮ የመንግሥት ሥራ አስፈጻሚ ሹመቶችንም አጽድቋል፡፡

የመስከረም ወር ዜና መጽሔታችን እነዚህንና ሌሎች ዓበይት ምክር ቤታዊ ውሳኔዎችን የምታስነብብ ይሆናል፡፡

መልካም ንባብ

መስከረም/ 2019 ዓ.ም

## ሹመት

7ኛው የኢፌዲሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በ1ኛ ዓመት የስራ ዘመኑ የምክር ቤቱን ምሥረታ ስነ ሥርዓ አካሂዷል።

በዚሁ ዕለት ምክር ቤቱ በህገ መንግስቱ አንቀጽ 55 /19 መሠረት የተከበሩ አቶ አሕመድ ሽዴን የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባኤ አደረጎ በሙሉ ድምጽ አጽድቋል። የተከበሩ አቶ አህመድ ሽዴ በምክር ቤቱ ፊት ቀርበው ቃለ-መሀላ ፈጽመዋል።





በተያያዘም የተከበሩ ወ/ሮ አየለች እሸቴን የምክር ቤቱ ም/አፈ ጉባኤ አድርጎ በሙሉ ድምጽ አጽድቋል።

የተከበሩ ወ/ሮ አየለች እሸቴ በምክር ቤቱ ፊት ቀርበው ቃለ- መሃላ ፈጽመዋል።





የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት
HOUSE OF PEOPLES REPRESENTATIVES OF THE FDRE

## ክቡር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ሆነው ተሰየሙ፤

7ኛው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት 1ኛ ዓመት የሥራ ዘመን በአካሄደው የምክር ቤቱ ምስረታ ሥነ ሥርዓት ክቡር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)ን የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር አድርጎ ሰይሟል።

ክቡር ዐቢይ አሕመድ(ዶ/ር) በምክር ቤቱ ፊት ቀርበው ቃለ መሃላ ፈጽመዋል።





ፕሬዘዳንት ታዬ አፅቀሥላሴ መስከረም 26 ቀን 2019 ዓ.ም የሕዘብ ተወካዮች እና ለፌዴሬሽን ምክር ቤቶች በአካሄዱት የጋራ መክፈቻ ሥነ ሥርዓት ላይ ተገኝተው የመንግሥትን የ2019 እቅድ አስመልክቶ ንግግር አድርገዋል።





ክቡር ፕሬዝዳንት ታዬ አፅቀሥላሴ በ2019 በጀት ዓመት በመንግሥት ለማከናወን የታቀዱ ቁልፍ ግቦችን ለምክር ቤቱ አቅርበዋል፡፡

•የሃገራችንን አጠቃላይ የኢኮኖሚ እድገት ወደ 10.1 በመቶ ማሳደግ፣

•የዋጋ ግሽበትን ወደ ነጠላ አኃዝ ዝቅ ማድረግ፣

•አጠቃላይ የታክስ ገቢን ከፍ ማድረግ፣

•የኤሌክትሪክ ሽፋንን ወደ 64 በመቶ ማሳደግ፣

•የጤና መድህን ሽፋንን ወደ 85 በመቶ ከፍ ማድረግ፣

•የተማሪዎች ምገባ ሽፋንን ወደ 70 በመቶ ማሳደግ፣

•በአረንጓዴ ልማት የደን ሽፋን አሁን ካለበት 26 በመቶ ከፍ ማድረግ፣

•ከ1.6 ሚሊዮን በላይ የውጭ ጎብኚዎች ኢትዮጵያን እንዲጎበኙ ማድረግ፣

•የውኃ ተጠቃሚነትን በስፋት ማሳደግ፣

•የመሶብ ዲጂታል አገልግሎት ማዕከላትን ቁጥር መጨመር እና

•ኢትዮጵያ የምታስተናግደውን 32ኛውን የአየር ንብረት ለውጥ ጉባኤ በስኬት ለማካሄድ ብቁ መሆን፡፡



የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት
HOUSE OF PEOPLES REPRESENTATIVES OF THE FDRE

7ኛው የኢፌዲሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በ1ኛ ዓመት የሥራ ዘመኑ መስከረም 27 ቀን 2019 ዓ.ም በአካሄደው 1ኛ ልዩ ስብሰባው በፌደራል መንግሥት አስፈጻሚ አካላት ስያሜ፣ አደረጃጀት፣ ስልጣንና ተግባር ለመወሰን የቀረበው ረቂቅ አዋጅ ላይ ተወያይቶ አጽድቋል፡፡







የመንግሥት ዋና ተጠሪ ሚኒስትር የተከበሩ አቶ ፍቃዱ ተሰማ የረቂቅ አዋጁን አስፈላጊነት አስመልክቶ ለምክር ቤቱ ማብራሪያ አቅርበዋል፡፡

የተከበሩ አቶ ፍቃዱ በማብራሪያቸው ከዚህ በፊት በነበሩት 22 አስፈፃሚ አካላት ላይ የቁጥር ልዩነት እንደሌለው ጠቁመው ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች በነበሩበት ይቀጥላሉ ሲሉ ገልጸዋል፡፡
ሁለት ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች ላይ ብቻ የስያሜ ለውጥ እንደተደረገና ሁለት ሚኒስትር መ/ቤቶች ደግሞ እንደ አዲስ ተቋቁመዋል፡፡

በዚህም መሠረት የቀድሞ "የባህልና ስፖርት ሚኒስቴር" የነበረው በአዲሱ "የወጣቶች እና ስፖርት ሚኒስቴር" በሚል እና ቀድሞ "የቱሪዝም ሚኒስቴር" የነበረው በአዲሱ "የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር" ሆኗል፡፡ የፕላንና ልማት ሚኒስቴር" የነበረው "የብሔራዊ ስትራቴጂ ሚኒስቴር" በሚል እና ቀድሞ

"የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር" የነበረው "የሎጂስቲክስ ሚኒስቴር" በሚል ስያሜያቸው መቀየሩን የተከበሩ አቶ ፍቃዱ ለምክር ቤቱ አስገንዝበዋል።

አክለውም በሚኒስቴር መ/ቤቶቹ ላይ ማሻሻያው ያስፈለገበት ምክንያት ይበልጥ ውጤታማ ለማድረግ እና ከተልዕኳቸው ጋር ለማጣጣም ነው ብለዋል።

በቀረበው ረቂቅ አዋጅ ላይ ከምክር ቤት አባላት ለተነሱ ጥያቄዎችና አስተያየቶች በክብርት ፍፁም አሰፋ (ዶ/ር) እና በክብርት ወ/ሮ ሃና አርአያሥላሴ ለምክር ቤቱ ምላሽና ማብራሪያ ሰጥተዋል።

በመጨረሻም ምክር ቤቱ ሰፊ ውይይት ከአካሄደ በኃላ የፌዴራል መንግሥት አስፈፃሚ አካላትን ስያሜ፣ አደረጃጀት፣ ስልጣንና ተግባር ለመወሰን የቀረበውን ረቂቅ አዋጅ አዋጅ ቁጥር 1440/2019 አድርጎ በሙሉ ድምጽ አጽድቋል።

## 7ኛው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በ1ኛ ዓመት የሥራ ዘመኑ መስከረም መስከረም 28 ቀን 2019 ዓ.ም በአካሄደው 1ኛ መደበኛ ስብሰባ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ክቡር አቶ ተመስገን ጥሩነህን ጨምሮ የ22 ሚኒስትሮችን ሹመት የውሳኔ ሀሳብ መርምሮ አፅድቋል።




በዚህም መሠረት የኢፌዲሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ክቡር ዐቢይ አሕመድ(ዶ/ር) እጩ ጠቅላይ ሚነስትርና ሚኒስትሮችን ለምክር ቤቱ አቅርበዋል።

1. ጌዲዮን ጢሞቴዎስ (ዶ/ር) ፦ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሚኒስትር
2.. አቶ አዲሱ አረጋ፦ የግብርና ሚኒስቴር ሚኒስትር
3. ፍጹም አሰፋ (ዶ/ር)፦የገንዘብ ሚኒስቴር ሚኒስትር





3. ፍጹም አሰፋ (ዶ/ር)፦ የገንዘብ ሚኒስቴር ሚኒስትር
4. አቶ መሃመድ እንድሪስ፦ የመከላከያ ሚኒስቴር ሚኒስትር
5. ብርሃኑ ነጋ (ፐ/ር)፦ የትምህርት ሚኒስቴር ሚኒስትር
6. ወ/ሮ ሃና አርአያሥላሴ፦ የፍትህ ሚኒስቴር ሚኒስትር
7. ወ/ሮ ያስሚን ወሀቢረቢ፦ የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር ሚኒስትር
8. ፍስሃ ይታገሱ (ዶ/ር)፦ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ሚኒስትር
9. ሀብታሙ ኢተፋ (ዶ/ር)፦ የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ሚኒስትር
10. ዶ/ር መቅደስ ዳባ፦ የጤና ሚኒስቴር ሚኒስትር
11. አቶ አወሉ አብዲ፦ የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር ሚኒስትር
12. ወ/ሮ ዓይናለም ንጉሴ፦ የገቢዎች ሚኒስቴር ሚኒስትር
13. አቶ በረከት ፍስሃ ጽዮን፦ የብሔራዊ ስትራቴጂ ሚኒስቴር ሚኒስትር
14. ወ/ሮ ሰላማዊት ካሳ፦ የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ሚኒስትር
15. ወ/ሮ ዓለምጸሃይ ጳውሎስ፦ የማዕድን ሚኒስቴር ሚኒስትር
16. አቶ ሳዳት ነሻ፦ የሎጅስቲክስ ሚኒስቴር ሚኒስትር
17. ወ/ሮ ሽዋት ሻንካ፦ የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳዮች ሚኒስቴር ሚኒስትር
18. አቶ ሙሳ አደም፦ የሰላም ሚኒስቴር ሚኒስትር
19. ወ/ሮ ፍሬሕይዎት ታምሩ፦ የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ሚኒስትር
20 . ኢንጅነር መሃመድ አብዱራሃማን፦ የከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስቴርሚኒስትር
21. ሱልጣን ወሊ (ዶ/ር)/(ኢ/ር)፦ የመስኖና ቆላማ አካባቢዎች ሚኒስቴር ሚኒስትር
22. አክሊሉ ታደሰ (ዶ/ር)፦ የወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር ሚኒስትር

የቀረቡት ዕጩዎች ለሕዝብ ለውጥና ለሀገር እድገት ቅድሚያ በመስጠት ከመቼውም ጊዜ በላይ ተግተው ሊሰሩ እንደሚገባም፣ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች የህዝብን ፍላጎትና ጥያቄ በቅርበት አዳምጠው ለመመለስ ዝግጁ ሊሆኑ ይገባል ሲሉ የምክር ቤት አባላት ጥያቄና አስተያየት ሰጥተዋል።

የኢፌዲሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ክቡር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ምላሽ ሲሠጡ ሁሉም ምክትል ጠቅላይ ሚንስትርን ጨምሮ እነዚህ የተሾሙት 22 ሚንስትሮች በተቻለ መጠን ሀይማኖትን፣ ፆታን እና የስራ ውጤታማነትን መሰረት ያደረገ ነው ሲሉ ከምክር ቤት አባላት ለተነሳላቸው ጥያቄና አስተያት ማብራሪያ ሰጥተዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በማብራሪያቸው "ስልጣን እንደ ኮፍያ ነው›› ለሀገር እድገትና ብልጽግና በትጋት የሚሰራ ባለስልጣን በክብር የሚቀመጥ ሲሆን፤ በአንጻሩ የሕዝብ አገልጋይነትን ወደ ጎን በመተው በስልጣን መቆየት እንደማይቻል አስረድተዋል።

ከቀረቡት ሚኒስትሮች መካከል ዘጠኝ ሚኒስትሮች ሴቶች ሲሆኑ ይህም በአፍሪካ የመጀመሪያ ሊሆን እንደሚችልና የፆታ ተሳትፎን ለማሳደግ ሴቶች በስራ ውጤታማ ሊሆኑ እንደሚገባም ጠቅላይ ሚኒስትሩ አክለው አስረድተዋል፡፡



ተሿሚዎች በትምህርት ዝግጅታቸውና ባካበቱት የስራ ልምድ መሰረት በየተመደቡባቸው ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች የላቀ ውጤት በማስመዝገብ የኢትዮጵያን የብልጽግና ጉዞ ለማሳካት የሚችሉ መሆናቸውን ለምክር ቤት አባላት አብራርተዋል፡፡

ምክር ቤቱ በጠቅላይ ሚኒስትር ክቡር ዐቢይ አህመድ (ዶ/ር) የቀረቡ እጩ የሚኒስትሮች ሹመት በሙሉ ድምፅ አፅድቋል፡፡

አድራሻ ( Adress)
ስልክ tel. 011-113-49-70 ነጻ ስልክ ጥሪFree call; 8557
ፖስታ ሳጥን ቁጥር P.O.Box: 80001
ኢ-ሜል: E-mail info@hopr.go.et
ድረ-ገጽ website: www.hopr.gov.et